# ምዕራፍ ሰባት

## ገንዘብ

### 7.1 ገንዘብን መደመርና መቀነስ

**የቡድን ሥራ**

1. የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ምን ይባላል?
2. ተማሪዎች እስከ አሁን የባለ ስንት ብር ኖት አይታችኋል?
3. በሳንቲም ደረጃ የትኞቹን የሳንቲም ዲናሮች ታውቃላችሁ?
4. የኢትዮጵያን የመገበያያ ሳንቲም ዲናሮች አይነት ዘርዝሩ።
5. የኢትዮጵያን መገበያያ የብር ኖቶች ዘርዝሩ።

**ገንዘብ** ማለት ሕዝቦች በመግባባት እቃዎችን ወይም አገልግሎትን የሚገዙበት የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ነው። የብሮቹና የሳንቲሞቹ የዋጋ መጠን የተለያዩ ናቸው። በመንግሥት የሚታተሙ ናቸው። በዚህም መሠረት **ባለ መቶ ብር፣ ባለ ሃምሣ ብር፣ ባለ አሥር ብር፣ ባለ አምስት ብር** እና **ባለ አንድ ብር የወረቀት ብር** ወይም **ኖቶች** አሉን። በሳንቲም ደረጃ ደግሞ **ባለ አንድ ብር፣ ባለ ሃምሣ ሳንቲም፣ ባለ ሃያ አምስት ሳንቲም፣ ባለ አሥር ሳንቲም፣ ባለ አምስት ሳንቲም** እና **በባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች** አሉን።



የ1 ብር ኖት



የ5 ብር ኖት


የ10 ብር ኖት


የ50 ብር ኖት


የ100 ብር ኖት



1ሳንቲም 5ሳንቲም 25 ሳንቲም 50 ሳንቲም 1 ብር

የኢትዮጵያ የመገበያያ የሳንቲም ዲናሮች

**ለምሳሌ፡-**

1. (ሀ) አንድ የመቶ ብር ኖት ስንት ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል?

 100 ብር = 2 ባለ ሃምሳ ብር ኖት ነው፡፡

 ምክንያቱም 2 × 50 ብር =100 ብር ስለሆነ



(ለ) የ50 ብር ኖት ባለ ስንት የአሥር ብር ኖት ይሆናል?



50 ብር = 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር

ስለዚህ 5 ባለ አሥር ብር ኖቶች አንድ ባለ ሃምሣ ብር ኖት ይሆናል ማለት ነው፡፡

(ሐ) የ10 ብር ኖት ባለ ስንት አምስት ብር ኖቶች ይሆናል?



10 ብር = 5 ብር + 5 ብር

ወይም 10 ብር = 2 × 5 ብር ይሆናል፡፡

10 ብር = 10 ብር ስለዚህ ሁለት ባለ አምስት ብር ኖቶች አንድ ባለ አሥር ብር ኖት ይሆናል ማለት ነው፡፡

© FDRE Ethiopia Not to be republished

መ. የ5 ብር ኖት ስንት ባለ አንድ ብር ኖት ይሆናል?



5 ብር = 1ብር + 1 ብር + 1 ብር + 1 ብር + 1ብር

☺ **አስተውሉ**

1. ሀ. አንድ የ100 ብር ኖት በ2 ባለ 50 ብር ኖቶች



ለ. አንድ የ100 ብር ኖት = በ10 ባለ 10 ብር ኖቶች



ሐ. አንድ የ100 ብር ኖት = 20 ባለ 5 ብር ኖቶች



መ. አንድ የ100 ብር ኖት በ100 ባለ 1 ብር ኖቶች ይመነዘራል::

2. እያንዳንዱ የብር ኖቶች በላያቸው ላይ በተጻፉት አሀዞች ልክ ዋጋ አላቸው:: በተጨማሪ እያንዳንዳቸው የተለያዩ **ቀለም**፣ **ቅርጽ** እንዲሁም **ስዕሎች** አሏቸው:: በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ለዩ::

3. ማንኛውም የመገበያያ ገንዘብ በአገሪቱ መንግሥት እውቅና (ባለቤትነት) ብቻ ታትመው ገበያ ላይ ይውላሉ::

4. የኢትዮጵያ ገንዘብ ምድቦች ብር እና ሳንቲም ናቸው፡፡ የተለያዩ አገሮች የመገበያያ ገንዘብ ምድቦች የተለያዩ ናቸው፡፡

**ምሳሌ፡-**

የ1ብር ኖት በስንት የ50 ሳንቲምና በስንት ባለ 25 ሳንቲም ዲናር ይመነዘራል?

1ብር = 100 ሳንቲም ነው፡፡

100 ሳንቲም = 2 × 50 ሳንቲም

= 50 ሳንቲም + 50 ሳንቲም (2 ባለ ሃምሳ ሳንቲም)

= 25 ሳንቲም + 25 ሳንቲም+ 25 ሳንቲም+ 25 ሳንቲም

= 4 × 25 ሳንቲም (አራት ባለ 25 ሳንቲም) ይሆናል፡፡



= 1 ብር ከ25 ሳንቲም

100 ሳንቲም = 1 ብር

ለ. 45 ብር – 13 ብር



ወይም

45 ብር
-13 ብር
32 ብር

4 ባለ 10 ብር ኖቶች እና 5 ባለ 1 ብር ኖቶች

## 7.2 ግብይት

**ተግባር 7.1**

1. ተማሪዎች አንድ እርሳስ እና እስኪሪብቶ በስንት ሳንቲም ትገዛላችሁ?
2. ላጲሳችሁን በስንት ባለ 10 ሳንቲሞች ገዛችሁ?
3. የእርሳስ መቅረጫችሁን በስንት ብር ወይም ሳንቲም ገዛችሁ? ተወያዩ፡፡
4. አንድ የስዕል ነጭ ወረቀት በስንት ሳንቲም መግዛት ትችላላችሁ?
5. ቤተሰቦቻችሁ ገበያ ወይም ሱቆች ሄደው ምን ምን ይገዛሉ? የሚገበያዩበት ገንዘብ ባለ ስንት የብር ኖቶች እና ሳንቲሞች ናቸው? ቤተሰብ በመጠየቅ በሳንቲም ሊገዙ የሚችሉትን የእቃዎች ዝርዝር ለብቻ በብር ኖቶች እና በሳንቲም ዲናሮች ሊገዙ የሚችሉትን የእቃ ዝርዝር ለብቻቸው በመለየት ዘርዝሩ፡፡ ተወያዩባቸው፡፡

### ምሳሌ፡-

ሀ. አንድ ብርቱካን 75 ሣንቲም ቢሸጥ አራት ተመሳሳይ ብርቱካኖች ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልገናል?

75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም



4 ሀምሳ ሳንቲሞች እና አራት 25 ሳንቲሞች

4 ሃምሳ ሳንቲሞች = 2 ብር 4 ባለ 25 ሳንቲሞች=1ብር

በጠቅላላው 2 ብር + 1 ብር = 3 ብር ያስፈልገናል፡፡

ለ. ከዚህ በታች በምስሉ ላይ የሚታዩት ሳንቲሞች ስንት ብር ናቸው?



2 ብር ከ65 ሣንቲም

1. አቶ ሳምሶን ገበያ ሄዶ ከአቶ አማረ በ1000 ብር ሁለት በጎችን ገዛ፡፡ አቶ ሳምሶን ለአቶ አማረ ስንት ባለ መቶ ብር ኖት መክፈል አለበት?

10 × 100 = 1000 ብር

10 ባለ መቶ ብር ኖቶችን መክፈል አለበት



## መልመጃ-7ሀ

*1. የሚከተሉትን ደምሩ፡፡*

1. ሀ. 10 ብር + 25 ብር
   ለ. 12 ብር + 5 ብር
   ሐ. 50 ብር + 6 ብር
   መ. 60 ብር + 40 ብር
   ሠ. 50 ብር + 50 ብር
   ረ. 100 ብር + 200 ብር

2. ሀ. 25 ሳንቲም + 75 ሳንቲም
ለ. 10 ሳንቲም + 40 ሳንቲም
ሐ. 35 ሳንቲም + 10 ሳንቲም
መ. 55 ሳንቲም + 25 ሳንቲም

*3. የሚከተሉትን ቀንሱ።*

1. ሀ. 25 ብር - 10 ብር
ለ. 50 ብር - 40 ብር
ሐ. 65 ብር - 15 ብር
መ. 70 ብር - 20 ብር

2 ሀ. 90 ሳንቲም - 80 ሳንቲም
ለ. 95 ሳንቲም - 15 ሳንቲም
ሐ. 100 ሳንቲም - 85 ሳንቲም
መ. 150 ሳንቲም - 100 ሳንቲም

*4. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ፍቱ።*

ሀ. አዝመራው ለሁለት ልጆቹ 10 ደብተሮች እያንዳንዳቸውን በ3 ብር ከሱቅ ቢገዛ በጠቅላላው ስንት ብር ከፈለ? በሳንቲም ሲመነዘርስ?

ለ. አልማዝ ከአቶ ሀሰን መደብር 1 ኪሎ ስኳር በ15 ብር፣ 2 ኪሎ ፓስታ በ30 ብር እና 1 ፓኬት ክብሪት በ4 ብር ገዛች። ወ/ሮ አልማዝ በጠቅላላው ስንት ብር ወጪ አደረገች?

ሐ. ሰብለወንጌል ተማሪ ነች። ለመመዝገቢያ 40 ብር እና ለግማሽ ዓመት የትምህርት ክፍያ 250 ብር ከፈለች። ሰብለወንጌል በጠቅላላ ስንት ብር ወጪ አደረገች?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**ሀ. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ሁሉም የኢትዮጵያ ብር ኖቶች በቅርጻቸው አንድ ዓይነት ናቸው።
2. የ100 ብር ኖት ከባለ 50 ብር ኖት ጋር እኩል ነው።
3. 100 ባለ 1 የብር ኖቶች በ2 ባለ 50 ብር ኖቶች ሊቀየሩ ይችላሉ።
4. 10 ባለ 100 ብር ኖቶች 1000 ብር ይሆናሉ።
5. 20 ባለ 5 ብር ኖቶች ከ1 ባለ 100 ብር ኖት ጋር እኩል አይደሉም።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች የትክክለኛውን መልስ ፊደል ምረጡ።**

1. 2 ባለ 100 ብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. 4 ባለ 50 ብር ኖቶች　　ሐ. 10 ባለ 10 ብር ኖቶች

   ለ. 8 ባለ አሥር ብር ኖቶች　　መ. 5 ባለ ሃምሳ ብር ኖቶች

2. ከ10 ባለ 10 የብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነውን ለዩ።

   ሀ. 2 ባለ 50 ብር ኖቶች　　ሐ. 10 ባለ 5 ብር ኖቶች

   ለ. 4 ባለ 10 ብር ኖቶች　　መ. ሁሉም መልስ ነው።

3. ከሚከተሉት አንዱ የመገበያያ ገንዘብ ምድብ አይደለም።

   ሀ. ብር　　ለ. ሳንቲም　　ሐ. ጨው　　መ. ሀ እና ለ

4. 95 ብር ስንት ባለ 10 ብር ኖቶች እና ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች ይኖሩታል? 95 ብር በስንት የባለ 5 ብር ኖቶች ይመነዘራል? 95 ብር በስንት የባለ አንድ ብር ኖቶች ይመነዘራል?

5. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ።

   ሀ. 6 የ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ለ. 10 የ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ሐ. 4 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   መ. 2 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ10 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ሠ. 4 የ100 ብር ኖቶች ስንት የ50 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ረ. 6 የ50 ብር ኖቶች ከስንት የ100 ብር ኖቶች ጋር እኩል ይሆናሉ?